የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ነጋሪት ጋዜጣ

AFAR REGION NEGARIT GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

10ኛ ዓመት ቁጥር 30 ሠመራ ሚያዚያ 3 ቀን / 1998 ዓ.ም	በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት	10th Year No. 30 Samara 11 April, ,2006

ማውጫ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

ቁጥር 30/1998 ዓ.ም ---------- ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር 30/1998 ዓ.ም

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

መግቢያ

በስራ ላይ ያለው የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት አንደኛው ለሌላኛው ተጠሪ ሆኖ እንዲዋቀር መደረጉ ለተጠያቂነት፣ ለስራ ጥራትና ቅልጥፍና አመች ያልነበር በመሆኑ፣

የአስፈፃሚ አካላት ም/ቤቱን አወቃቀርና የእየርከኑን አካላት የስራ ግንኙነት ይበልጥ ውጤታማና ለመስራት የሚያስችለውን ምቹ ሁኔታ መፍጠር ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት ተሻሽሎ ባወጣው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 47 ንዐስ አንቀጽ 3/ሀ/ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለውን አውጿል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

አንቀጽ 1

አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት አስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 30/1998 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ 2

ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ

1. ህገ መንግስት ማለት የ 1994 ዓ.ም የተሻሻለው የአፋር ክልል ህገ መንግስት ነው።
2. ቢሮ ማለት የክልልለ መስተዳድር ምክር ቤት አባል ሆኖ በዚህ አዋጅ የተቋቋመ የክልል መንግስቱ አስፈፃሚ መስሪያ ቤት ነው።
3. የቢሮ ኃላፊ ማለት በዚህ መ/ቤት የበላይ ኃላፊ ሆኖ እንዲያገለግል በህገ መንግስቱ መሠረት የተሾመ ማንሀናውም የተፈጥሮ ሰው ማለት ነው።
4. ምክር ቤት ማለት የክልሉ መስተዳድር /ካቢኔ/ ምክር ቤት ማለት ነው።

ክፍል ሁለት

ስለ ርዕሰ መስተዳድሩ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩና የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ምክር ቤት

አንቀጽ 3

ስለ ርዕሰ መስተዳድሩ ስልጣንና ተግባር፦

የአፋር ብሔራዊ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ስልጣንና ተግባር በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 59 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው ይሆናል።

አንቀጽ 4

ስለ ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ ስልጣንና ተግባር፦

የአፋር ብሔራዊ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ስልጣንና ተግባር በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 60 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው ይሆናል።

አንቀጽ 5

ስለ መስተዳድር ም/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

የአፋር ክልል መስተዳድር ም/ቤት ስልጣንና ተግባር በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 56 ድንጋጌዎች ስር የተመለከተው ይሆናል።

አንቀጽ 6

ውክልና ስለመስጠት

በሁኔታዎች አጋጣሚ የክለሉ ርዕሰ መስተዳድርና ም/ርዕሰ መስተዳድሩ በአንድ ወቅት በማይኖሩበት ጊዜ የአመራር ስለጣኑ ክፍት እንዳይሆን የክልሉን ህገ መንግስት በማይቃረን መልኩ ሁለቱም ከካቢኔ አባላቱ አንዱን በም/ርዕሰ መስተዳድርነት መወከል ይችላሉ።

አንቀጽ 7

የክልል መስተዳድር ም/ቤት አባላት

1. የክልል መስተዳድር ም/ቤት ከዚህ በታች የተመለከቱት አባላት ይኖሩታል።

   ሀ. ርዕሰ መስተዳድሩ

   ለ. ም/ርዕሰ መስተዳድሩ

   ሐ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ስር የተመለከቱትን ቢሮዎች የሚመሩ የቢሮ ኃላፊዎች

   መ. በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰየሙ ሌሎች ባለስልጣናት

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/ሐ/ ስር የተመለከተው ማንኛው የቢሮ ኃላፊ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ በተሰየ ሁኔታ በጽሑፍ ካልወከለ በስተቀር በሹመት ቅድሜያ ያለው ምክትል የቢሮ ኃላፊ በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ ይሳተፋል።

አንቀጽ 8

ስለ ክልል ርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት፦

1. የክልል ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 61/2/ መሠረት የመስተዳድሩ ም/ቤት ጽ/ቤት በመሆን ጭምር ያገለግላል።
2. የጽ/ቤቱ ኃላፊም በዚህ አዋጅ መሠረት በቢሮ ኃላፊ ማዕረግ የሚሾም ሆኖ፦

   ሀ. የካቢኔውን ጉዳይ በበላይነት ያስፈጽማል።

   ለ. በካቢኔው ም/ቤት ስብሰባዎች ላይ ያለድምጽ ይሳተፋል። ሃሳብና አስተያየት ይሰጣል።

   ሐ. ወደፊት የሚወሰነው እንደተጠበቀ ሆኖ የርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት ኃላፊ ስልጣንና ተግባር በአዋጅ ቁጥር 16/1994 አንቀጽ 7 ድንጋጌዎች ስር የተገለፀው ይሆናል።

አንቀጽ 9

ስለ ኮሚቴዎች መቋቋም

የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ስልጣንና ተግባሩን ለመወጣት ይረዳው ዘንድ እንደ አስፈላጊነቱ ለስራው አጋዥ የሚሆነው ኮሚቴ ሊያዋቅር ይችላል።

ክፍል ሶስት

ስለ ቢሮዎች በጠቅላላው

አንቀጽ 10

መቋቋም

የሚከተሉት ቢሮዎች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል።

1. የአቅም ግንባታ ቢሮ

2. የአርብቶ አደር ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ
3. የአስተዳደርና የፍትህ ጉዳዬች ቢሮ
4. የንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርትና ኢንቨስትመንት ቢሮ
5. የስራና ከተማ ልማት ቢሮ
6. የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ
7. የህዝብ አደረጃጀት የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ
8. የፍትህ ቢሮ
9. የትምህርት ቢሮ
10. የአደጋ መከላከል ዝግጁነት ቢሮ
11. የሴቶች ጉዳይ ቢሮ
12. የጤና ጥበቃ ቢሮ
13. የውሃ ሃብት ልማት ቢሮ
14. የባህል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ

አንቀጽ **11**

የቢሮዎች የውል ስልጣንና ተግባር፦

እያንዳንዱ ቢሮ ከዚህ በታች የተገለፁት የጋራ የውል ስልጣን ይኖራቸዋል።

1. የፌዴራውንና የክልሉን ሕጐች በክልሉ ውስጥ በስራ ላይ ያውላሉ፣
2. ክልል አቀፍ ፖሊሲዎችን ስትራቴጂዎችንና ሕግጋትን ያመነጫሉ፣ የስራ እቅድና የማስፈፀሚያ በጀት ያዘጋጃሉ፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላሉ፣
3. የዎታ እኩለነት መርና ልዩ ትኩረት በመስጠት የሴቶችን ህገ መንግስታዊ ተጠቃሚነት ያረጋግጣሉ፣
4. በሕግ መሠረት ውሎችን ይዋዋላሉ ስምምነቶችን ያደርጋሉ ይከሳሉ ይከሰሳሉ የንብረት ባለቤት ይሆናሉ፣
5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዞንና ወደ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ያላቸው የክልሉ መንግስት ቢሮዎች ወይም አስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች፦
   ሀ. በክልሉ የተቀናጀ ልማት እንዲመጣ በስራቸው የሚገኙ የዞንና የወረዳ መስሪያ ቤቶችን በተስተካከለ አደረጃጀት ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በሰው ኃይል አቅማቸውን ይገነባል፣
   ለ. የክልሉን የልማት ፖሊስና እስትራቴጂ ማዕከል ባደረገ መልኩ የተቀናጀ ልማት እንዲረጋገጥ በስራቸው የሚገኙ የዞንና የወረዳ መስሪያ ቤቶችን የእቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን የከታተላሉ፣ ይቆጣጠራሉ፣ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣሉ።
   ሐ. በዞንና በወረዳ ከሚገኙ ቅርንጫፍ አስፈፃሚ መ/ቤቶች ጋር የመረጀና የሪፖርት ልውውጥ ስርዓት በመዘርጋት በወረዳ ስለሚገኙ መ/ቤቶች ወቅታዊና የተሟላ ሪፖርት ለክልሉ መስተዳድር ም/ቤትና ለርዕስ መስተዳድሩ ያቀርባሉ።
6. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 ስር በተደነገገው መሠረት የመስተዳድር ም/ቤት አባላትም ሆኑ በስራቸው ሌሎች የክለሉ አስፈፃሚ አካላትን ያቀፉ ቢሮዎች፦

ሀ. በስራቸው ያሉትን ጽ/ቤቶች ወይም ኮሚሽኖች ወይም የባለስልጣን መ/ቤቶች በበላይነት ይመራሉ ስራቸውን ያስተባብራራሉ አደረጃጀታቸውንና የስራ ንሮግራሞቻቸውን መርምረው ለሚመለከተው የክልሉ መንግስት ለአካላት እንዲቀርብ ያደርጋሉ፣

ለ. በስራቸው መንግስታዊ የልማት ድርጅቶች ካሉም በህግ መሠረት ይቆጣጠራሉ። የልማት አጋር ሆነው መስራታቸውን ያረጋግጣሉ።

7. በዚህ አዋጅና በሌሎች ሕጐች የተሰጡትን ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ያውላሉ።
8. ስለ ስራቸው ክንውን በወቅቱ ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር መ/ቤት ሪፖርቶችን ያቀርባሉ።

አንቀጽ 12

የቢሮ ኃላፊዎች ተጠሪነትና ኃላፊነት

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1/ለ/ እና /ሐ/ መሠረት ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩን ጨምሮ የክልል መስተዳድር ም/ቤት አባላት የሆኑ ቢሮ ኃላፊዎች ተጠሪነት ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ይሆናል።
2. የቢሮ ኃላፊዎች የሚመሩትን ቢሮዎች ይወክላሉ ስልጣንና ተግባራትን በስራ ላይ ያውላሉ።
3. ለየቢሮዎቻቸው በተፈቀደው በጀትና የስራ ንሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋሉ።
4. የቢሮዎቻቸው ውጤታማ የስራ አመራር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላሉ ያረጋግጣሉ።

አንቀጽ 13

የምክትል ቢሮ ኃላፊዎች ተጠሪነትና ተግባር፦

እያንዳንዱ ምክትል የቢሮ ኃላፊ

1. በቢሮ ኃላፊው ተለይቶ የማሰጠውን ቴክኒካል /ሞያዊ/ ስራዎችን ይሰራል።
2. የቢሮ ኃላፊው በማይኖርበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ የሰራል።
3. በአንድ ቢሮ ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ምክትሎች በሚገኙበት ጊዜ ከቢሮ ኃላፊው በተለይ የጽሑፍ ውክልና የተሰጠው ሰው መኖሩ ካልተረጋገጠ በስተቀር አርሱን ተክቶ ቢሮውን የማመራው በሹመት ቀደምትነት ያለው ምክትል የቢሮ ኃላፊ ይሆናል።
4. ም/ቢሮ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለየቢሮው ኃላፊ ይሆናል።

አንቀጽ 14

የሌሎች አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነትና በየደረጃው የሚቋቋም ስለመሆኑ፦

1. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለአቅም ግንባታ ቢሮ ይሆናል።

   ሀ. የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

   ለ. የስራ አመራር ማሰልጠኛ ኢንስትቲዩት

   ሐ. የአፋርኛ ቋንቋ ማበልፀጊያ ማዕከል

   መ. የሲቪል ሠርቪስ ንሮግራም ጽ/ቤት

2. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለአስተዳደርና ፍትህ ጉዳዮች ቢሮ ይሆናል።

   ሀ. የፊትህ ቢሮ

ለ. የፖሊስ ኮሚሽን

ሐ. የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት

መ. የሚሊሻ ጽ/ቤት

ሠ. የወሰን ጉዳይ ጽ/ቤት

3. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለአርብቶ አደር ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ይሆናል።

ሀ. የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ምርምር ኢንስቲቲዩት

ለ. የሕብረት ስራ ማህበራት ማደራጂያና ማስፋፊያ ጽ/ቤት

ሐ. የግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም

መ. የገጠር ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ማዕከል

4. የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ባለስልጣን ተጠሪነቱ ለውሃ ሃብት ልማት ቢሮ ይሆናል።

5. የወጣቶችና ስፖርት ጉዳይ ጽ/ቤት ተጠሪነቱ ለሕዝብ አደረጃጀት ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ይሆናል።

6. የገጠር መንገድ ባለስልጣን ተጠሪነተቱ ለስራና ከተማ ልማት ቢሮ ይሆናል።

7. የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ተጠሪነት ለክልሉ ርዕስ መስተዳድር ይሆናል።

1. የማዕድንና ኢነርጅ ሃብት ልማት ጽ/ቤት
2. የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት
3. የናማሌፈን ከሠም ተንዳሆሁለገብ ኘሮጀክት ጽ/ቤት

ክፍል አራት

የቢሮዎች ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት

አንቀጽ **15**

የአቅም ግንባታ ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. ለክልሉ አቅም ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ የአቅም መገንቢያ ተቋማት እንዲገነቡ ያደርጋል፣
2. የአቅም ግንባታን በማጐልበት ረገድ ለወረዳና ለቀበሌ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል አቅም ግንባታ በተመለከተ በየመስተዳድር እርከኑ የሚደረገውን እንቅስቃሴ ይከታተላል መረጃ ይይዛል ያጠናቅራል ይህንንም ማረጋገጥ ይችል ዘንድ አስፈላጊውን የግንኙነት መሠረት ይዘረጋል፣
3. የክልሉን የአቅም ግንባታ ፍላጐት ቅደም ተከተል ለመለየት የሚያስችል ጥናቶችን ያካሂዳል፣
4. አቅምን ለመገንባት የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ኘሮግራሞች ኘሮጀክቶችን ይቀርፃል ቀልጣፋ የኘሮግራሞችና የኘሮጀክቶች አፈፃፀም የሚኖርበትን ስልት ይቀይሳል ስራ ላይ ያውላል።
5. የነባር አቅም ግንባታ ኘሮግራሞችን አፈፃፀም ይከታተላል ይገመግማል ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአፈፃፀምን ስልት እንዲኖራቸው ችግር ያለባቸውን አንዲሻሻሉ ያደርጋል፣
6. የአዳዲስ ፖሊሲዎችና ኘሮግራሞችን አፈፃፀም ይከታተላል ይገመግማል ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአፈፃፀም ስልት እንዲኖራቸው እንዲሻሻሉ ያደርጋል፣

7. ለአቅም ግንባታ ለፀደቁ ኘሮግራምና ኘሮጀክቶች ማስፈፀሚያ የሚሆን የፋይናንስ የቴክኒክ ድጋፍ የሚገኝበትን መንገድ እያጠና ስራ ላይ ያውላል የተገኘውን ድጋፍ ለኘሮግራሙና ኘሮጀክቶቹ ያከፋፍላል የሪሶርስ አጠቃቀሙን በየጊዜው እያጠናና እየገመገመ እንደ አስፈላጊነቱ ያሸጋሽጋል ያዛውራል ተገቢ የማሻሻያ እርምጃዎችን ይወስዳል፣
8. በመንግስት አስተዳደር ውስጥ የሚታየውን የሰው ሃይል ልማት አስተዳደርና አጠቃቀም ተቋማዊ አደረጃጀትና አሠራር ዘዴዎች ድክመት ክትትል በማድረግ የግልጽነት ተጠያቂነት፣ የህጋዊነትና የውጤታማነት መርሆችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወስዱ ያደርጋል አፈፃፀማቸውን ይከታተላል ያረጋግጣል፣
9. በክልሉ ያልተማከለ የአስተዳደር ስርዓት እንዲጐለብት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
10. በክልሉ ውስጥ የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጅ አጠቃቀም የሚስፋፋበትንና የሚጠናከርበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል።

አንቀጽ **16**

የአርብቶ አደር ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ

ቢሮው ከዚህ የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የክልሉን አርብቶ አደር የኑሮ ሁኔታ የተሻለ ለማድረግ ፖሊሲዎችን ያመነጫል የስራ ኘሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ያስፈፅማል፣
2. በክልሉ ውስጥ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የግብርናና የገጠር ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣
3. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የደንና የዱር እንስሳት ጥበቃና አጠቃቀም ሕጐችን ያዘጋጃል አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣
4. በእርሻ ስራ ለተሰማሩ አርብቶ አደሮች የማሰጡ የኤክስቴሽን አገልግሎቶች ያስፋፋል ይመራል ይቆጣጠራል፣
5. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የመስኖ ልማት ስራዎች እንዲስፋፋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ያበረታታል ድጋፍ ይሰጣል፣
6. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የገጠር መሠረተ ልማት አገልግሎቶች እንዲስፋፋ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
7. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የብድር አገልግሎቶች ለአርብቶ አደሩና ለከፊል አርብቶ አደሩ የሚቀርቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
8. በግብርናው መስክ ለተሰማሩ የግል ባለሃብቶች የተሟላ ድጋፍ ይሰጣል፣
9. በግብርና ልማት ላይ ተጽዕኖ የሚኖራቸውን ወቅታዊ ሁኔታዎች ይከታተላል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ይዘረጋል፣
10. ወደ ክልሉ በሚገቡና ከክልሉ በሚወጡ ዕፅዋት አዝርዕት እንሰሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ላይ ተገቢውን የኳራንቲን ቁጥጥር ያደርጋል፣
11. የእንስሳትና የዕፅዋት በሽታዎች ወረርሽኝና ተዛማች ተባዬችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል፣
12. ለግብርናና ለገጠር ልማት እንቅፋት የሚሆኑ ተግባሮችን በመለየት የማፈቱበትን መንገድ ያመቻቻል፣
13. የግብርና ልማትን ለማፋጠንና የገጠር ቴክኖሎጂን ለማሻሻል የሚረዱ የማሰልጠኛ ተቋማትንና ማዕከላትን ያቋቁማል፣ ይመራል፣

14. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የሰብል፣ የእንስሳትና የገጠር ቴክኖሎጂ ብዜት ማዕከላትን ያስፋፋል፣ ያስተዳድራል፣ አዳዲሶችም እንዲቋቋሙ ያደርጋል፣
15. በምርምር የተገኙ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን ያቀርባል፣ ያለምዳል የምርምር ማዕከላት ስራዎችን ይቆጣጠራል ይከታተላል፣
16. የተቀናጀ ልማትን በማስፈፀም ረገድ ወረዳዎችን ያስተባብራል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣
17. በክልሉ የረጅም የመካከለኛና የአጭር ጊዜ አቅድ ውስጥ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚካሄዱ ስራዎች እንዲካተቱ ያደርጋል ሲፈቀድም ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል።
18. የምግብ ዋስትና ኘሮግራሞችን በበላየነት ይመራል ይቆጣጠራል፣
19. የተቀናጀ የምግብ ዋስትና ኘሮጀክቶች ኘሮግራሞች ማስፈፀሚያ የሚውል ፈንድ /ሌላ ሃብት/ ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከህብረተሰቡ የሚገኙበትን ሁኔታ ያጠናል ያመቻቻል የተገኘው ፈንድና ሃብት በክልሉ መንግስት ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በሕዝባዊ ተቋማት ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
20. የግብርና ልማቱን በገበያ እንዲመራና ቀልጣፋ የግብርና ግብዓትና ምርት የግብይት ስፖግት እንዲፈጠር ያደርጋል የምርት ግብዓቶችን አስመልክቶ የገበያ ፍላጐት ትንበያ ጥናት ያካሂዳል የግብርና ምርቶች ገበያ የሚስፋፋበትን ዘዴ ይቀይሳል። ተግባራዊ ያደርጋል፣
21. በገጠር ልማት እንቅስቃሴ የገጠር ሴቶች ተሳትፎ እንዲጐለብት ያደርጋል የልማቱ ተጠቀሚ በማድረግ የተሻለ ኑሮ የሚኖሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል። በዚሁ ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ይሰራል።

አንቀጽ 17

የአስተዳደርና የፍትህ ጉዳዮች ቢሮ

ቢሮው ከዚህ የሚከተሉት ዝርዝር ስለጣንና ግባራት ይኖሩታል፣

1. በክልሉ ውስጥ ሕግና ስርዓት መከበሩንና የሕብረተሰቡ ሰላምና ደህንነት መጠበቁን ይከታተላል ያረጋግጣል፣
2. ወንጀል እንዳይፈፀም አስቀድበሞ በመከላከል የክልሉን ሕዝብ ሰላምና ደህንነት ያስጠብቃል፣በወንጀል መከላከሉ ተግባር ላይም ህብረተሰቡ ተሳታፊ እንዲሆንና የራሱን ሰላምና ደህንነት እንዲያስከብር ያበረታታል፣ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣
3. የህግ ታራሚዎች የህብረተሰቡን ሰላምና ፀጥታ በማወክ ሁኔታ መጠበቃቸውን፤ በአግባቡታርመው ወደ ማህበራዊኑሮ መመለሳቸውንናብቁዜጎች ሆነው መውጣታቸውን ይከታተላል ለዚሁም ተገቢ እርምጃዎችን ያረጋግጣል።
4. በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የሕግ አስከባሪ አካላት ዲሞክራሲያዊ አመለካከት ለማጐልበትና በሕገ-መንግስቱም ሆነ በሰብአዊ መብቶች ረገድ ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ ይሠራል፣
5. በክልሉ ውስጥ ከየእርከኑ አስተዳደሮች መካከል የሚሱ አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ የሚፈቱበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
6. ከአጐራባች ክልሎች ጋር በሚያዋስኑ አካባቢዎች የሚሱ አለመግባባቶች በሰላማዊ መንገድ የሚፈቱበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣

7. የክልሉን ሰላምና ፀጥታ መጠበቁን በማረጋገጥ ረገድ አግባብ ካላቸው ክፍሎች ጋር ተባብሮ ይሠራል በአስተዳደራዊ ወሰኖች፣ በሕዝብ ደህንነትና በፀጥታ ስራ ጉዳዮች ረገድ ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግስትና የሌሎች ክልሎች አካላት ጋር ግንኙነቶችን ያደርጋል፣
8. የክልሉ የፍትህ ስርዓት እንዲሻሻል ጥናቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል ያስተባብራል።

አንቀጽ **18**

የንግድ ኢንድስትሪ ትራንስፖርትና ኢንቨስትመንት ቢሮ

ቢሮው ከዚህ የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. የክልሉን የንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርትና ኢንቨስትመንት ክፍለ ኢኮኖሚ የሚመራበት ፖሊሲና ስትራቴጂ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፣
2. በክልሉ ውስጥ የንግድና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን ይመራል ይቆጣጠራል የኢንዱስትሪና የትራንስፖርት አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያበረታታል እንዲጐለብት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣
3. የንግድ ኢንዱስትሪ የትራንስፖርትና ኢንቨስትመንት ክፍለ ኢኮኖሚው የሚመራበትን ደንቦችን ያዘጋጀል በሚመለከተው አካል ሲፀድቅለትም በስራ ላይ ያውላል የወጡ ሕጐች ደንቦችና መመሪያዎችን በክልሉ መተግበራቸውን ያረጋግጣል፣
4. ለሌሎች አግባብ ላላቸው አካላት የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉን መንግስት የትራንስፖርትና መገናኛ አገልግሎቶችን እንዲሰሩ እንዲሻሻሉና እንዲጠገኑ ያደርጋል፣
5. በክልሉ በሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ለሚካሄድ የንግድና የኢንቨስትመንት ስራዎች የኢንዱስትሪ እደ ጥበባት በሕዝብ ማመላለሻና መገናኛ አገልግሎቶች መስኮች የሚከናወኑትን ተግባራት በበላይነት የመራል ይከታተላል፣
6. የሕዝብና የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ማህበሮችን ይመዘግባል በማህበር የሚቀርቡለትን የስምሪት ኘሮግራም ያፀድቃል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣
7. በክልሉ መንግስት ውስጥ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን ይመዘግባል በነዚሁ ላይ የቴክኒክ ምርመራ ያደርጋል፣ መንጃ ፈቃድ ይሰጣል፣
8. በክልል መንግስት ውስጥ የትራንስፖርትና የመገናኛ ዓይነቶች ተደጋጋፊው የሚሄዱበትንና በተቀነባበረ ሁኔታና በሚገባ በጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
9. በክልሉ መንግስት ውስጥ የመሠረታዊ የንግድ እቃዎች አገልግሎቶች ስርጭት አግባብ ባለው አካል የተወሰነው የዋጋ ተመን መከበሩን ይቆጣጠራል፣
10. የሚቀርቡለትን የኢንቨስትመንት ማመልከቻዎች መርምሮ ፈቀድ ይሰጣል አስፈላጊውን ገቢ ይሰበስባል፣
11. በባለሀብቶችና ጉዳዮች በሚመለከታቸው ሌሎተ የክልሉ መስተዳድር አካላት መካከል የኢንቨስትመንት ተግባራትን ያስተባብራል ይቆጣጠራል፣
12. በክልሉ የኢንዱስትሪና የአርብቶ አደር የልማት ውጤቶች እንዲታወቁ ኢግዚቢሽን እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣
13. የኢንዱስትሪ ኘሮጀክቶችን እያመነጨ በማዕከላዊ መንግስት ስራ ላይ ሊውሉ የሚገባቸውን ለሚመለከተው የሚኒስቴር መስሪያ ቤት ያስተላልፋል ሌሎችም በክልል ደረጃ እንዲጠኑና በስራ ላይ እንዲውሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

14. በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን የሀብት ክምችትና የኢንቨስትመንት እድል መረጃዎች ያሰባስባል ያጠናክራል መረጃዎችን ለባለ ሀብቶች ያሰራጫል ተጨባጭ የኢንቨስትመንት ኘሮጀክቶችንም ለእነዚህ ባለሀብቶች ያስተዋውቃል።

አንቀጽ 19

የስራና ከተማ ልማት ቢሮ

ቢሮው ከዚህ የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. የስራና የከተማ ልማት ቢሮን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣
2. የሕንፃ ኮድ፣ የዲዛይንና የኮንስትራክሽን ስራ ደረጃዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፣
3. በክልሉ መንግስት በጀት ለሚሰሩ የመንግስት ኮንስትራክሽኖች የስራ ውሎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣
4. በክልሉ መንግስት በጀት የሚከናወኑ የመንግስት ኮንስትራክሽን በተገባለት ውል መሠረት የጥራት ደረጀው የጊዜና የዋጋ ገደቦች ተጠብቀው መሠራቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቁጥጥር እንዲኖር ያደርጋል በበላይነትም ይቆጣጠራል፣
5. በከተሞች ውስጥ ለሚካሄድ ኢንቨስትመንት በከተማ ቦታና የኮንስትራክሽን ስራዎች ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
6. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በከተሞች ውስጥ ለሚካሄድ የግል ኪራይ ቤቶች ግንባታ የኢንቨስትመንት የስራ ፈቃድ ይሰጣል፣
7. በክልል መንግስቱ ባለቤትነት ስር የሚገኙ የከተማ ቤቶችን በሚመለከት ቴክኒካዊ ድጋፍ ይሰጣል፣
8. ለከተሞች ኘላን ዝግጅት የሚረዳ ጥናቶች ያካሂዳል ከሚመለከታቸው የማዕከላዊ መንግስት አካላት ጋር አስፈላጊውን ትብብር ያደርጋል የከተሞችን ኘላን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ዝርዝር ኘላኖች እንዲዘጋጁ ያደርጋል አፈፃፀማቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል የከተሞችን ደረጀ በየጊዜው እያጠና ይወሰናል፣
9. የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ከአቅሙ ጋር የተመጣጠኑ ቤቶችን ሠርቶ እንዲጠቀመ ሁኔታዎችን እንዲመቻቹ ያደርጋል፣
10. የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት እንዲቋቋሙ ያበረታታል ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ይቀይሳል፣
11. በክልል ከተሞች ውስጥ የመኖሪያ ቤት ችግርን ለማቃለል የቁጠባ ቤቶች እንዲሰሩና እንዲከራዩ ሁኔታዎችን ያመቻቻል ያበረታታል፣
12. በክልሉ የሚገኙ ማዘጋጃ ቤቶችን በበጀት በእቅድና በከተማ ኘላን አዘገጃጀትና አፈፃፀም በሰው ኃይል ስምሪት በአስተዳደርና ገቢ አሰባሰብ ረገድ ይከታተላል ይቆጣጠራል የቴክኒክ ሙያ ድጋፍ ይሰጣል።

አዋጅ 20

የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

ቢሮው ከዚህ የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

1. የክልሉ መንግስት አካላት የአገሪቱን የፋይናንስ ፖሊሲዎች ሕጐች ደንቦችና መመያዎችን ተከትለው መስራታቸውን ይቆጣጠራል፣
2. በክልሉ መንግስት አካላት እየተዘጋጁ የሚቀርቡትን የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ጥያቄዎች መርምሮ የክልሉን የተጠቃለለ ዓመታዊ በጀት በማዘጋጀት ከአስተያየቱ ጋር ለክልሉ መንግስት ምክር ቤት ያቀርባል የተፈቀደውን በጀት ያስተዳድራል፣

3. የክልል መንግስቱን የፋይናንስ ክንውንና የገንዘብ ይዞታ የሚያሳይ ጠቅላላ መግለጫ በወቅቱ ለክልል መስተዳደር ምክር ቤት ያቀርባል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ በጀት አዘጋጅቶ ያስወስናል፣
4. የክልሉ መንግስት ከሀገር ውስጥ የብድር ምንጮች የሚያገኛቸውን ብድሮች በክልል መንግስት ስም ይፈራረማል ብድሮችንም እየተቆጣጠረ ያስተዳድራል፣
5. የክልል መንግስቱን የእቃና የአገልግሎት ግዥና አጠቃቀም መመሪያ ያዘጋጃል ተግባራዊነቱን ይቆጣጠራል፣
6. በአገሪቱ የልማት ስትራቴጂ ላይ የተመሠረተና በክልሉ መንግስት የሚፈፀም የረጅም የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የልማት እቅድ ያዘጋጃል ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣
7. ከፌዴራል የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጋር በተገባው ውል መሠረት በክልሉ የሚካሄዱትን የልማት ትብብር ስራዎችን ያስተባብራል በልማት ትብብር ኘሮጀክቶች ዝግጅት ስራ ይሳተፋል፣
8. በክልሉ መንግስት እንዲሰሩ የሚያስችል ፈቃድ ያላቸውን መንግስታዊ ያልሆኑ የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ስራ ያስተባብራል ስለስራቸው አፈፃፀም ብቃታቸውን ይቆጣጠራል፣
9. የክልል መንግስቱን ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ይመሰርታል በክልሉ መንግስት አካላት በስራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፣
10. የማናቸውንም የክልሉ ወንግስት አካላት የሂሳብ መዛግብቶች ሠነዶችና ማስረጃዎችን ይመረምራል፣
11. ከአገሪቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ አንፃር በክልሉ የግል ክፍለ ኢኮኖሚ ተሳትፎ እንዲበረታታ ድጋፍ ሰጪ የሆኑ አመልካች እቅድ ያዘጋጃል፣
12. በሌላ የክልሉ መንግስት አካል ስር የማይተዳደር ወይም ጥቅም ላይ ያልዋለ የክልሉ መንግስት ንብረቶች ኃላፊ ሆኖ ያስተዳድራል፣
13. ህዝብና ልማትን የሚመለከቱ መረጃዎችን በማሰባሰብ ለክልሉ መስተዳደር ምክር ቤትና ለሚመለከተው ለፌዴራል መንግስት አካል ያስተላልፋል፣
14. አግባባ ባለው ህግ መሠት ከማናቸው የገቢ ምንጭ የሚገኙ የክልል መንግስቱ ገቢ በሚገባ መወሰኑን መሰብሰቡና ሂሳቡ መያዙን ያረጋጋጣል የክልሉን የገቢ መሠረት የሚስፋፋበትንና ፍትሃዊ የገቢ ስርዓት የሚኖርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
15. ገቢን በሚመለከት በበላይነት ይቆጣጠራል ይመራል፣
16. የክልሉን የረጅም የመካከለኛና የአጭር ጊዜ የልማት እቅድ ለማዘጋጀትና ይህንኑ የሚረዳ የኢኮኖሚ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል የኘላን ሜቶዶሎጂና መመዘኛዎችን ያዘጋጃል፣
17. የክልሉን የተፈጥሮ ሀብት የምርት የሕዝብ የሳይንስና ቴክኖሎጅ ስርጭት የአገልግሎት መረጃዎችን ያሰባስባል ያጠናክራል ለሚመለከታቸው ያስተላልፋል፣
18. የየሴክተሩን እቅድ አፈፃፀም እየገመገመ የተቀነባበረ ሪፖርት በየሶስት ወሩ ለክልል መስተዳድር ም/ቤት ያቀርባል፣
19. የአገሪቱ የስነ ህዝብ ፖሊሲ በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል። ይህንኑ በተመለከተ የሚካሄዱ ምርምሮችን እንዲበረታታ ያደርጋል። ለፖሊሲው ተግባራዊነቱ እንደ አስፈላጊቱ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል ተግባራቸውንም ይከታተላል።

የሕዝብ አደረጃጀትና የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ

ቢሮው ከዚህ የሚከተሉት ዝርዝር ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ህብረተሰቡ ራሱን በልዩ ልዩ ማህበራት እያደራጀ በልማት ስራው ተሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ ያመቻቻል የህብረተሰቡ ተሳትፎ በስርዓት የሚመራበትን ስልት ይቀይሳል፣
2. ማህበራት የእርስ በእርስ ተሞክሮ ልውውጥና መደጋገፍ እንዲያደርጉና በቅንጅት እንዲንቀሳቀሱ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል፣
3. ስራ አጥነትንና ሌሎች ማህበራዊ እድገት ጠንቆች ተወግደው ዜጐች አምራች ኃይል እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፣
4. የሃገሪቱ የሠራተሃሃ ማህበራዊ ጉዳይ ፖሊሲዎችና ህጐች በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣
5. አሠሪና ሠራተኛን በሚመለከት የወጡ ህጐች ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል፣
6. የሠራተኞችን ደህንነትና ጤንነት ለመጠበቅ የወጡ የስራ ሁኔታ ደረጃዎችና የመከላከያ ዘዴዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ይቆጣጠራል፣
7. በብሔራዊ ክልሉ የግዛት ወሰን በየድርጅቱ የሚቋቋሙትን የሠራተኛና አሰሪ ማህበራት ይመዘግባል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣
8. የህብረት ስምምነት ድርድሮችና የስራ ክርክሮች በህግ የተዘረጋውን ስርዓት ተከትለው በተቀላጠፈ ሁኔታ ፈፃሜ እንዲያገኝ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል የህብረት ስምምነቶችን ይመዘግባል፣
9. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ በስራ ላይ ስለተሰማራው የሰው ኃይልና ስለሞያው አመዳደብ ጥናት ያደርጋል፣
10. በክልሉ ውስጥ ስራ ፈላጊዎችና ክፍት የስራ መደቦች እንዲመዘገቡና ስራና ሠራተኛ እንዲገናኝ የሚያስችሉ አርምጃዎችን ይወስዳል፣
11. ስለክልሉ የሰው ኃይልና የስራ ስምሪት ስለሠራተኞች ያሰባሰባል ያጠናቅራል ከትንተና ጋር ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፣
12. አግባባ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ የሚገኙ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞችን ለመርዳትና መልሶ ለማቋቋም የሚያስችሉ ኘሮግራሞችን ያዘጋጃል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣
13. የማህበራዊ ኑሮ ጠንቆች እንዲወገዱ የክልሉን ህብረተሰብ ጥረት ያስተባብራል አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣
14. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የቤተሰብና የሕፃናት ደህንነት እንዲጠበቅ ለማድረግና የጋብቻ ስርዓትን ለመንከባከብ የወጡ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ያደርጋል።

አንቀጽ **22**

የፍትህ ቢሮ

ቢሮው ከዚህ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፦

1. የሕግ ጉዳዮችን በሚመለከት የክልል መንግስቱን ይወክላል የሕግ አማካሪ ሆኖም ይሰራል፣
2. በክልሉ መንግስት በሚገኙ ፍ/ቤቶች ስልጣን ክልል ስር በሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮች የክልሉን መንግስት በመወከል ይከራከራል፣

3. የሕዝቡን እንዲሁም የክልሉን መንግስት መብትና ጥቅም ለማስከበር በፌዴራልና በክልል ፍርድ ቤቶች በንኖውም የዳኝነት ሰጭ አካል ወይም በሽምግልና ጉባኤ ክስ ይመሰርታል። ክስ እንዲመሰረት ያደርጋል ወይም ጣልቃ በመግባት ይከራከራል እንደነገሩ ሁኔታም ተከላካይ በመሆን ይቀርባል፣
4. በክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ የመንግስት ደንቦችና መመሪያዎች መከበራቸውን እንደዚሁም በክልሉ መንግስት ወይም በክልሉ መንግስት አካላት ላይ የሚቀርቡትን የፍትህ ብሔር ክሶችና ጥያቄዎች በአግባቡ መያዛቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሪፖርት እንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል፣
5. በክልሉ መንግስት አካላት ጥያቄ ሲቀርቡለት የሕግ ረቂቆችን በማዘጋጀትና የሕግ አስተያየት በመስጠት ይረዳል፣
6. በማረሚያ ቤትና በማረፊያ ቤት የተያዙ ወይም የታሰሩ ሰዎች የእስርና የአያያዛቸውን ሕጋዊነት ይከታተላል የሰብአዊ መብታቸው እንዲከበር ያደርጋል። ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተያዙ ሰዎች ወደ ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ያደርጋል፣
7. የወንጀል ድርጊት ምስክሮች አንደ አስፈላጊነቱ ተገቢውን የሕግ ጥበቃ እንዲያገኝ ያደርጋል።
8. እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መከራከር ለሚችሉ ጠበቆች ፈቃድ ይሰጣል ይቆጣጠራል ይሰረዛል፣
9. ከሰብአዊ መብት አጠባበቅ አንፃር የሕዝቡን ንቃተ ሕግ ለማዳበር በተለያዩ ዘዴ የሕግ ትምህርት ስልጠና በሚመለከት በክልሉ ውስጥ ለሚገኙ ዳኞች አቃቢያነ ሕግና ፖሊሶች የስልጠናን ኘሮግራሞችን ያዘጋጃል ይመራል የሙያ ሰርቲፊኬት ይሰጣል፣
10. የየደረጃውን አቃቢ ህግ በበላይነት ይመራል ይቆጣጠራል፣
11. በክልሉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ በፍታ ብሔር ጉዳይ ሊከራከርላቸው የሚችል የሕግ ክፍል ለሌላቸው መስሪያ ቤቶች ነገረ ፈጅ በሆነ በመደበኛ ፍርደ ቤቶች በመገኘት ይከራከራል የመስሪያ ቤቶቹ የፍትሐ ብሔር ጉዳይ ወኪል በመሆንም ያገለግላል ለዚህ ስራም ብቃት ያለው የሰው ኃይል እንዲደራጅ ያደርጋል፣
12. በክልሉ መንግስት ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ወንጀል ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ እንዲደረግ ያዛል በቂ ምክንያት ሲኖር የተጀመረ ምርመራ እንዲቆም ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወን ያደርጋል በህግ መሠረት የወንጀል ክስ ያነሳል፣
13. የክልሉ የፍትህ አስተዳደር ሥርዓት የሚሻሻልበትን መንገድ ያጠናል በአግባቡ ተደራጅቶ ለክልሉ ነዋሪ ህዝብ ተገቢውን አገልግሎት የሚሰጥበትን ሁኔታ ያመቻቻል ጉዳዮ ከሚመለከታቸው አካላትም ጋር በጋራ ይሠራል፣
14. በክልሉ ውስጥ የውል የውክልና የማስረጃ ምዝገባዎችን ይሰራል አላማቸው ለትርፍ ያልሆኑ በክልሉ ለሚንቀሳቀሱ ማህበራት ፈቃድ ይሰጣል ይሰርዛል፣
15. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የወንጀል መከላከል የሚረዱ ጥናቶች ያካሂዳል ወንጀል የሚቀነስበትን ስልት ይቀይሳል፣
16. በወንጀል ድርጊት ከባድ ጉዳት ደርሶባቸው በክልሉ ፍርድ ቤቶች ክስ ለመመስረትና ለመከራከር አቅም ለሌላቸው ግለሰቦች መብታቸውንና ጥቅማቸውን ለማስከበርና ካሳ እንዲያገኙ በፍትሐ ብሔር ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ይከራከራል፣
17. የክልሉ ሕጐች ከፌዴራል ሕጐች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋጋጣል በየጊዜው አዲስ የወጡትን የክልሉንም ሆነ የፌዴራል ህጐችን እንዲሁም ማሻሻያዎችን እየተከታተለ ያሰባስባል፣ ያስጠርዛል፣ ህጐችና በማጠቃለል የኮዲፊኬሽን ስራ ይሰራል።

አንቀጽ 23

ትምህርት ቢሮ

ቢሮው የሚከተሉትን ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፦

1. **በአገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ መሠረት የክልሉን የትምህርት ስልጠና እቅድና ኘሮግራም ያዘጋጃል ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፣**
2. **ትምህርትን በክልል አቀፍ ደረጃ ለማስፋፋት የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል ለተግባራዊነታቸውም ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣**
3. **የክልሉ የትምህርት ጥራት በአገር አቀፍ የተወሰነውን እስታንዳርድ የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፣**
4. **የአገሪቱን የትምህርት ፖሊሲና እስታንዳርድ ተከታትሎና የክልሉንና የአካባቢ ሁኔታዎችን በማገናዘብ የክለሉን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና እንደ አስፈላጊነቱ የአፀደ ሕፃናት ስርዓት ትምህርት ያዘጋጀል ያጠናል ይገመግማል በስራ ላይ ያውላል፣**
5. **በክልሉ ለትምህርት የደረሱ ሁሉ የመማር እድል የሚያገኙበትን ስልት ይቀይሳል መሠረተ ትምህርት ለሁሉም እንዲዳረስ ያደርጋል፣**
6. **በየደረጃው ለማስተማር ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎች ማሟላታቸውን ያረጋግጣል መምህራንና የትምህርት ባለሙያዎችን ያሰለጥናል እንዲሰለጥኑም ያደርጋል፣**
7. **በአገር አቀፍ ደረጃ ተዘጋጅተው ለክልሉ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡትን ፈተናዎችን ተከታትሎ ያስፈፅማል፣ በክልሉ ደረጃ ተዘጋጅተው የሚሰጡትን ፈተናዎችንና የምስክር ወረቀቶች ብቃት ያረጋግጣል፣**
8. **ለትምህርት ስራ አስፈላጊ የሆኑ መፅሐፍትና ሌሎች የትምህርት መሳሪያዎች እንዲሟሉ ያደርጋል፣**
9. **የክልሉን የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና በክልል ደረጃ የሚቋቋሙ መለስተኛ ኮሌጆች ያደራጃል ያስተዳድራል፣**
10. **ለትምህርቱ ኘሮግራም ማስፈፀሚያ የሚሆን ኘሮጀክቶችን ያዘጋጃል ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፣**
11. **የክልሉ ትምህርት ኘሮግራሞች በሬዲዮና በሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች እንዲደገፉ ያደርጋል፣**
12. **የትምህርትን ስራ ለማሻሻል የሚያስችሉ ጥናቶችና ግምገማዎች ያካሂዳል በአገር አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ ጥናቶች ይሳተፋል አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣**
13. **የትምህርት መረጃዎችን ይሰበስባል ያጠናቅራል ለሚመለከታቸው አካላትም ያስተላልፋል፣**
14. **ለትምህርት ስራ አስፈላጊ የሆነውን ድጋፍ ለማግኘት እንዲቻል ህብረተሰቡን ያስተባብራሉ።**

አንቀጽ 24

የአደጋ መከላከልና ዝግጅነት ቢሮ

ቢሮው ከዚህ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

1. **በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ምክንያት የሚደርስ አደጋ ለመከላከል የሚያስችሉ ፖሊሲዎችና ስልቶችን ያቅዳል፣ ሲፈቀድም አግባባ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር በስራ ላይ ያውላል፣**
2. **አግባብ ካላቸው የክልሉ መንግስት አካላት ጋር በመተባበር አደጋ ለመከላከል የተቀየሱ ፖሊሲዎችና ስልቶችን በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣**

3. ከክልሉ መንግስት በሚሰጥ መመሪያ መሠረት ከአገር ውስጥ ማንኛውም አይነት ድጋፍ ይጠይቃል የእርዳታ ግንኙነትና አስተዳደርን በሚመለከት በፌዴራልና በክልል መንግስት በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ከእርዳታ ሰጭዎች አካላት ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፣
4. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አደጋ ሊመጣ የሚችልበትን ምክንያት አስቀድሞ ያጠናል፣ ያሳውቃል፣ አደጋው እንዳይደርስ ጊዜያዊና ዘላቂ የመከላከል እርምጃ ይወስዳል፣ ወይም እንዲወስድ ያደርጋል፣
5. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አደጋ በሚደርስበት ጊዜ የአደጋው አይነት መጠንና ስፋት እያጠና ሊወሰድ የሚገባውን እርምጃ ቁምር ለክልሉ መንግስት ያሳውቃል፣ እርዳታ የሚደረግበትን ቅደም ተከተል ይወስናል፣
6. ማንኛውም ዓይነት እርዳታ ይመዘግባል ለተረጅው በወቅቱ በትክክል እንዲዳረስ ያደርጋል፣
7. የእርዳታ ኘሮግራሞች ማስፈፀሚያ የሚያስፈልጉ ልማት ነክ ኘሮጀክቶችን ዝግጅትና አፈፃፀም ያስተባብራል፣
8. በክልሉ መንግስት እንዲሰሩ የሚያስችል ፈቃድ ያላቸው መንግስታዊ ያልሆኑ የግል የእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ስራ ያስተባብራል። ስለስራቸው አፈፃፀምና ብቃታቸውን ይቆጣጠራል፣
9. ዓላማውን ለማስፈፀም ከተለያዩ አካላት ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፣
10. ለሚመለከታቸው አካላት በየጊዜው ሪፖርት ያቀርባል።

አንቀጽ 25

የሴቶች ጉዳይ ቢሮ

የሴቶች ጉዳይ ቢሮ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

1. በክልሉ ውስጥ የሴቶችን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚረዱ ሃሳቦችን ያመነጫል፣ የማስፈፀሚያ ስልቶችን በመቀየስ ለተግባራዊነቱ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፣
2. በክልሉ መንግስት አካላት የሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ የልማት ኘሮግራሞች፣ ኘሮጀክቶች፣ እቅዶች እና ሪፖርቶች የስርዓተ ፆታን ጉዳይ ለማካተት የሚያስችላቸውን ስልት በመንደፍ አስፈላጊውን ክትትል ያደርጋል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣ ተፈፃሚነቱንም ያረጋግጣል፣
3. ሴቶች በክልሉ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በንቃት ለመሳተፍ የማያስችሏቸውን እድሎች የተመቻቹላቸው መሆኑን ያረጋግጣል፣
4. በሴቶች ላይ የሚቃጡ መድልዎችንና የሚፈፀሙ ጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በጥናት በመለየት እነዚሁ የሚወገዱባቸውን የመፍትሔ ሃሳቦችን ያመነጫል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣
5. ሴቶች ለዘመናት በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው ምክንያት የደረሰባቸውን
6. የተለያዩ የክልሉ መንግስት አካላት ሴቶችን በውሳኔ ሰጪ ቦታዎች በመመደቡ ረገድ በቂ ትኩረት ስለመስጠታቸው ይከታተላል።
7. ሴቶች እንፍላጐታቸውና እንደየችግሮቻቸው አይነት ተደራጅተው ለመብቶቻቸው ለጥቅሞቻቸው መከበር እንዲታገሉና ችግሮቻቸውን ማስወገድ እነዲችሉ ያበረታታል ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
8. ብሔራዊው የሴቶች ፖሊስ ተግባራዊ እንዲሆን በክልል አቀፍ ደረጃ ይከታተላላ ያስተባብራል፣

9. በዝቅተኛ የኑሮ ደህንት ላይ የሚገኙ የሴቶችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚረዱ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ ያስጠናል፣ ኘሮግራሞችንና ኘሮጀክቶችን በመቅረጽ ተግባራዊ ያደርጋል ለዚሁ ዓላማ ለሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችም አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፣
10. የእናቶችና የሕፃናት ደህንነት ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ያጠናል፣ ከሚመለታቸው አካላት ጋር በመተባበርም ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣
11. መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ከተለያዩ የማህበረሰብ ተቋማትና ከሴቶች ማህበራት ጋር ሴቶችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ዙሪያ ተባብሮ ይሰራል።

አንቀጽ **26**

የጤና ጥበቃ ቢሮ

ቢሮው ከዚህ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል

1. በክልሉ ውስጥ የጤና አገለግሎቶች እንዲስፋፉ ያደርጋል።
2. የሃገሪቱን የጤና ፖሊሲ መሠረት በማድረግ የክልል ሕዝብ ጤና የሚጠበቅበትን እቅድና ኘሮግራም ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፣
3. ለሕዝብ ጤና አጠባበቅ የወጡ ህጐች ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል።
4. የክልሉን ኗዋሪ ሕዝብ ፍላጐት መሠረት በማድረግ በየደረጃው የጤና ድርጅቶች የፋናትና ምርምር ማዕከላትንና ማሰልጠኛ ተቋማትን ያደራጃል ያስተዳድራል።
5. በክልሉ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ መድሃኒቶችንና የሕክምና መሳሪያዎችን ይመዘግባል ይቆጣጠራል።
6. በሃገር ውስጥ ባለሃብቶችና ድርጅቶች ለሚቋቋሙ ጤና ጣቢያዎች ክሊኒኮች የምርመራ ድርጅቶችና መድሃኒት ቤቶች ፈቃድ ይሰጣል። በሃገር አቀፍ ደረጃ የወጣውን መስፈርት ጠብቀው መስራታቸውን ይቆጣጠራል።
7. በክልሉ ውስጥ በሕዝብ ጤና አገልግሎት ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎች የተወሰነውን ደረጃ ማሟላታቸውን ያረጋግጣል ይቆጣጠራል።
8. በክልሉ ውስጥ የሚያገለግሉ መለስተኛና መካከለኛ የጤና ባለሙያዎችን ያሰለጥናል።
9. ፍቱንነታቸው የተረጋገጠ የባህል መድሃኒቶችና የህክምና ዘዴዎች ከዘመናዊው ህክምና ጋር ተዋህደው በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል ባለሞያዎችን ያደራጃል ያበረታታል።
10. የጤና ፖሊሲውን መሠረት አድርጐ የክልሉ ሕዝብ በሽታዎችን በመከላከል ላይ በስፋት የሚሳተፋበትን ዘዴና ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይል ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል።
11. ለጤና አገልግሎቱ መስፋፋት አስፈላጊ የሆኑ የግንባታ ስራዎችን ያቅዳል ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል።
12. የሕዝብን ጤና ለመጠበቅ በሚደረግ የኳራንቲን ቁጥጥር ይሳተፋል።
13. በምግብ እጥረት ወይም አለመመጣጠንና ብክለት ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያግዙ ስልቶችን ይቀይሳል ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል።
14. የምግቦችንና መጠጦችን ንጽህና ይቆጣጠራል ለጤና ተስማሚነታቸውንም ያረጋጋጣል።

አንቀጽ **27**

የውሃ ሃብት ልማት ቢሮ

ቢሮው ከዚህ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

1. የውሃ ሃብት አስተዳደርን በሚመለከት በፌዴራሉና በክልሉ መንግስት የወጡ ሕጐችን ደንቦችንና መመሪያዎችን በክልሉ ውስጥ መከበራቸውን ያረጋግጣል ይቆጣጠራል።
2. በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ተፋሰሶችና ንውሳን ተፋሰቦች የውሃ ሃብት ክምችትና ስርጭት ያጠናል መረጃዎችን ይሰበሰባል ያደራጃል ይያዛል ይተነትናል በወቅቱ ለሚመለከታቸው ያሰራጫል ከሌሎች ጋር በመተባበር በሚካሄዱ የውሃ ሃብት ጥናቶች ላይ ይሳተፋል እንዲጠኑም ያደርጋል።
3. የክልሉ ውሃ ሃብት አስተዳደር ሁለንተናዊ አቅም በሚገባ ተገንብቶ በቅንጅት እንዲከናወን የሚመለታቸው አካላት ያስተባብራል።
4. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የውሃ ሃብት በልዩ ልዩ የግልጋሎት አይነቶች መካከል ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መከፋፈሉንና በጥቅም ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል።
5. የጥናትና ምርምር ኘሮጀክቶችን ጨምሮ የክልሉን የውሃ ሃብት በሚመለከት የውሃ ጉድጓዶችን ለመቆፈር የተፋሰስ ልማት ስራዎችን የፍሳሽ ማስወገድ ወይም የድሬነጅና የመስኖ እንዲሁም የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድቦችንና ሌሎች የውሃ ስራዎችን ለመገንባት ለመጠገንና በጥቅም ላይ ለማዋል ጥያቄ ሲቀርብለት አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር ፈቃድ ይሰጣል ያድሳል ይሰርዛል።
6. የውሃ ሃብት አስተዳደርን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ክልል አቀፍ ፖሊሲዎችን ስትራቴጂካዊ እቅዶችን መመሪያዎችን ስታንዳርዶችንና ማንዋሎችን ያዘጋጀል ያሰራጫል ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል።
7. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የውሃ ተቋማት ደረጃውን የጠበቀ ዘላቂና ተፈላጊ አገልግሎት ይሰጡ ዘንድ ለኦኘሬሽንና ለጥገና ስራዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት ድርጅታዊ አቅማቸው የሚጐለብትበትንና የውሃ ተጠቃሚዎች ማህበራት የሚጠናከሩበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።
8. የውሃ ስራዎችን በተመለከተ በራሱ አነሳሽነትም ሆነ አግባብ ካላቸው አካላት ጥያቄ ሲቀርብለት ዲዛይኖችን ይሠራል እንዲሠሩ ያደርጋል።
9. በመስኩ የሙያ ብቃት ማረጋገጫና በውሃ አካላት የመጠቀም ፈቃድ ይሠጣል ለዚህም ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ይሰበሰባል።
10. የክልሉን የውሃ ታሪፍና የወጭ አመላለስ በተመለከተ ወጥና ፍትሐዊነት ያለው የታሪፍ የወጪ ተመላሽ አወሳሰን ስርዓት ተቀርፆ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል ጥናቶችን ያካሂዳል እንዲካሄዱም ያደጋል።
11. በክልሉ ውስጥ ለልዩ ልዩ ግልጋሎቶች የማውል ውሃ የተወሰነው የጥራት ደረጃ እንዲሁም ለልዩ ልዩ ፍሳሾች የተወሰነው የጤናማነት ደረጃ መጠበቁንና በስራ ላይ መዋሉን ይቀጣጠራል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በፊዚካል በኬሚካል በባዮሎጂካል የምርመራ ዘዴዎች ተጠቅሞ ፍተሻ በካሄድ ውሃው እንዲታከም ያደርጋል፣
12. የሜትሮሎጂና የሃይድሮሎጂ መረጃዎችን በሚመለከታቸው አካላት በመሰብሰብ በመተንተንና በማሰራጨት ለልማት ስራ እንዲውል ያደርጋል።
13. የውሃ ሃብትን በመጠበቅ ረገድ በተለይም ክልል ዘለል የሆኑ የውሃ አካላትን በሚመለከትና በክልሉ ውስጥ በፌዴራል መ/ቤቶች አማካይነት ለሚካሄዱ ስራዎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል።

14. በውሃ አካላት ላይ የሚደረገው ሕገ ወጥ የልማት እንቅስቃሴ ይከታተላል አስጊ የቆሻሻ ክምችት እንዳይፈፀምና የውሃ ብክለት እንዳይደርስ የኘሮጀክት ሃሳቦችን በመገምገም ተስማሚ የሆኑትን ያፀድቃል። የውሃ አካላት ደህንነት መጠበቁንና በአግባብ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋጋጣል።

15. የንፁህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት ከሳንቴሽን ስራዎች ጋር ተቀናጅቶ እንዲካሄድ ያደርጋል

16. ከመስኖ መሠረተ ልማት ጋር በተያያዘ ሊመጡ የሚችሉ የአካባቢ ተፅዕኖዎችን መከታተል ሊከሰቱ የሚችሉ እንደ ውሃ ወለድ በሽታ የውሃን አካባቢ ብክለትና የመሳሰሉ አደጋዎችን ለመቆጣጠር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይሠራል፣

17. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በተለይም በአርብቶ አደሩ ዘንድ የመስኖ እርሻና የመስኖ ግጦሽ ልማት እንዲለመድ የሚያበረታታ ስልት መቀየስ ለዚህ የሚረዱ ኘሮግራሞችን ይነድፋል ተግባራዊነታቸውን ይከታተላል፣

18. ለመጠጥ ውሃና ለመስኖ ልማት ፈንደ ያፈላልጋል አጠቃቀሙን በበላይነት ይቆጣጠራል፣

19. የመጠጥ ውሃና የመስኖ ውሃ አገልግሎት ዋጋዎችንና የታሪፍ ሐሳቦችን እያጠና ለመስተዳድር ም/ቤት ያቀርባል ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፣

አንቀጽ 28

የባህል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ

ቢሮው ከዚህ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

1. የክልሉ ሕዝብ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች እንደዚሁም በክልሉ የሚደረጉ አይት እንቅስቃሴዎችን በዜና ማሰራጫዎች ያሰራጫል። በአጠቃላይ የክልሉ መንግስት ቃል አቀባይ በመሆን ይሰራል።
2. በክልሉ መንግስት የሚቋቋሙ የመገናኛ ብዙሃንን ያደራጃል ይመራል ይቆጣጠራል።
3. ባህል፣ ኪነጥበብ፣ ስነ ጥበብና የፈጠራ ችሎታ እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያደርጋል።
4. በፌዴራል መንግስት የሚወጣውን መመሪያ ተከትሎ በክልል የሚገኘውን ታሪካዊ ቅርሶች ተፈልገው እንዲገኙ እንዲጠበቁ እንዲጠኑ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከሚመለታቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሠራል።
5. በክልሉ ውስጥ የሕዝብ ቤተ መፃሐፍትና ሙዚየሞች እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ ያደጋል።
6. የክልሉ ብሔረሰብ ታሪክና ባህል ተመዝግቦ እንዲያዝ ቋንቋውም እንዲዳብርና እንዲስፋፋ ያደርጋል።
7. የአገሪቱን የቱሪዝም ፖለሊሲን መሠረት በማድረግ በክልሉ ውስጥ የቱሪስት አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ያበረታታል።
8. የክልሉን የቱሪዝም እድገት ለማፋጠን የሚረዱ ጥናቶች ያካሂዳል።
9. በክልሉ በሃገር ውስጥ ባለሃብቶች ለሚካሄዱና ከሆቴሎች አገልግሎት ውጭ ላሉ የቱሪስት አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ፈቃድ ይሰጣል። ይቆጣጠራል።
10. ለክልሉ ባህል ቱሪዝምና ማስታወቂያ ስራዎች እድገት ሌሎች አስፈላጊ ተግባሮችን ያከናውናል።

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 29

ስለሌሎች አስፈፃሚ አካላት

በዚህ አዋጅ ውስጥ ስልጣንና ኃላፊነታቸው ያልተገለጹ የክልሉ አስፈፃሚ አካላትና ሌሎች ተቋማት ስልጣንና ተግባር በተቋቋሙበት ሕግ በተደነገገው መሠረት የተገለፀው ይሆናል።

ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 ስር የሠፈሩት ሌሎች ስልጣንና ተግባራቸውን የሚወሰን ሕግ ያልወጣላቸው አስፈፃሚ አካላትና ተቋሞች ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣው የየተቋማቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ይወሰናል።

አንቀጽ 30

የአስፈፃሚ አካላት ቅርንጫፍ በየደረጃው የሚቋቋሙ ስለመሆኑ

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋሙ አካላት በክልሉ ውስጥ እንደስፈላጊነቱ በዞን በወረዳ ወይም በሁሉም እርከኖች ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ሊኖራቸው ይችላል።
2. በየትኛውም እርከን የሚገኝ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ቅርንጫፍ ስልጣንና ተግባር በዋናነት በክልል ደረጃ ለቢሮዎች የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ስራ ላይ ማዋል ይሆናል።
3. የቅርንጫፍ መስሪያ ቤቱ ተጠሪነት በየደረጃው ለሚገኝ መስተዳድር ጽ/ቤት እና ለቢሮ ይሆናል።

አንቀጽ 31

የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጐች

1. የሚከተሉት ሕጐች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።
   ሀ/ የአፋር ብ/ክ/መንግስት አስፈፃሚ አካላት ለማቋቋምና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 15/1994 በዚህ አዋጅ ተሸሯል።
   ለ/ የኢንቨስትመንት ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 5/1991 እና አዋጅ ቁጥር 23/1996 እንደተሻሻለ በዚህ አዋጅ ተሸሯል።
   ሐ/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ህግ ደንብ መመሪያና የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ 32

መብቶችና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ

1. በአዋጅ ቁጥር 15/1994 አንቀጽ 17 ለእንስሳትና የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃ ቢሮ የተሰጡት መብቴችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለአርብቶ አደር ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ ተላልፈዋል።
2. በአዋጅ ቁጥር 15/1994 አንቀጽ 10 ስር ተደንግገው የነበሩት የንግድና ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ማስተባበሪያ ቢሮ መብቴችና ግዴታዎች እንደ አግባብነታቸው በዚህ አዋጅ ለተቋቋሙት ለንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርትና ኢንቨስትመንት ቢሮ እንዲሁም ለስራና ከተማ ልማት ቢሮ ተላልፈዋል።
3. በአዋጅ ቁጥር 15/1994 ተቋቁሞ የነበረው የሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመው ለሴቶች ጉዳይ ቢሮ ተላልፏል።

አንቀጽ 33

የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋሙት አስፈፃሚ አካላት በሚገባ እስኪደራጁ ድረስ በስራ ላይ ያሉትንና አግባብነት ያላቸውን ሕጐች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በክልሉ ውስጥ ለሚቀጥሉት ሶስት ወራት ያህል ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል።

2. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በአዋጅ ቁጥር 15/1994 ዓ.ም አና በሌሎች ህጐች ለቀድሞው የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ተሰጥተው የነበሩት ስልጣንና ተግባራት ከዚህ አዋጅ እና ከተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት ድንጋጌዎች ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት እንደገና ለተደራጀው ለክልሉ መስተዳድር ም/ቤት እንደተሰጡ ተቆጥሮ ይሰራባቸዋል።

አንቀጽ 34

ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጠን

በዚህ አዋጅ መሠረት፡-

1. የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ይህን አዋሁደ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።
2. የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ካቢኔው የሚያወጣቸውን ደንቦች ሙሉ ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው ዝርዝር መመሪያዎች የማውጣት ስልጣን አለው።

አንቀጽ 35

አዋጅ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሠመራሚያዚያ **3** ቀን **1998** ዓ.ም

እስማኤል አሊ ሴሮ

የአፋር ብ/ክ/መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር